# የእንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ መብት ፡ በኢትዮጵያ ።*

## በፒተር ፡ ዊንሺፕ ። **

የእንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ መብትን ፡ የሚመለከት ፡ አንድ ፡ ልዩ ፡ ሕግ ፡ እንደ ሚታወጅ ፡ እ.አ.አ. የ፲፱፻፷ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቢያመለክትም ፡ እንኳ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ይህንን ፡ ሕግ ፡ አላወጀም ፤ እንዲሁም ፡ ከተረቀቀው ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ በስተቀር ፡ ተስማሚ ፡ የሆነውን ፡ ረቂቅ ፡ ሕግ ፡ አላዘጋጀም ።[1] ሆኖም ፡ ሠፊ ፡ የሆነ ፡ ሕግ ፡ ያለመኖር ፡ ያስከተለው ፡ ታላቅ ፡ ጥፋት ፡ የለም ፤ እስከ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የተፈጠሩት ፡ ወይም ፡ ከጥቅም ፡ ላይ ፡ የዋሉት ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ እና ፡ የእንዱስትሪ ፡ ፍልሰማዎች ፡ ቁጥር ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ነበር ። በተጨ ማሪም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሕግ ፡ አስተሳሰቦች ፡ መጥተው ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ጥቂት ፡ ሰዎ ችን ፡ የንግድ ፡ ምልክቶችንና ፡ በኢንዱስትሪ ፡ በኩል ፡ የሚገኙትን ፡ የተፈለሰሙ ፡ ጥበቦች ፡ እንዲጠበቁ ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።[2] ነገር ፡ ግን ፡ የእንዱስትሪ ፡ መብትንና ፡ እንዲሁም ፡ በንግድና ፡ በእንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ በሚገኘው ፡ በንግድ ፡ ምልክትና ፡ በእንዱስትሪ ፡ ባለቤትነት ፡ መዝገብ ፡ እንዲመዘገብ ፡ የሚጠይቁ ፡ ማመልከቻዎችና ፡ የእንዱስትሪ ፡ ባለሀብትነትን ፡ የሚመለከቱ ፡ ክሶች ፡ እየበዙ ፡ ስለሄዱ ፡ መንግሥቱ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ የእንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ ባለሀብትነት ፡ ሕግ ፡ በዝርዝር ፡ ለማ ውጣት ፡ ማሰብ ፡ አለበት ። በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ለማሳየት ፡ የምንፈልገው ፡ ምንም ፡ እንኳ፡ አንዳንድ ፡ ክፍሎች ፡ በእንዱስትሪ ፡ በኩል ፡ የፈለሰሙትን ፡ ጥበቦች ፡ ለመጠበቅም ፡ ቢችሉ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ያለው ፡ የሕግ ፡ ምስቅልቅል ፡ አዲስ ፡ ሕግ ፡ ወጥቶ ፡ እንዲያ ብራራው ፡ እንደሚያስፈልግ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ዓላማ ፡ ከግቡ ፡ ለማድረስ ፡ የሚያስ ችለው ፡ ከሁሉ ፡ የተሻለው ፡ ዘዴ ፡ ከአሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የንግድ ፡ ሕጉ ፡ ያመ ለከተውን ፡ ሰፊ ፡ የሆነና ፡ ሁሉን ፡ የሚያመለክት ፡ ሕግ ፡ ማዘጋጀትና ፡ ማወጅ ፡ ነው ።

## ፩. ዓለም—አቀፍ ፡ (ኢንተርናሲዮናል) ፡ ውሎች ።

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኙ ፡ የእንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ መብቶች ፡ ምንጭ ፡ የሚ ሆኑ ፡ የዓለም—አቀፍ ፡ ውሎች ፡ ናቸው ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ በቀጥታ ፡ እንዱስ ትሪ ፡ ንብረት ፡ መብቶችን ፡ የሚመለከተው ፡ በዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ እና ፡ በኢትዮጵያ ፡ መካከል ፡ የተፈፀመው ፡ የወዳጅነትና ፡ የኤኮኖሚ ፡ ግንኙነት ፡ ውል ፡ ብቻ ፡ ነው ።[3] የዚሁ ፡ ውል ፡ አንቀጽ ፡ ፱ ፡ ንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ፡ እንደሚለው ፡—

---

* ገጽ ፡ ፪፻፳፫ ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ የምጣድ ፡ ክስና ፡ ገጽ ፡ ፪፻፴፩ ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ክስ ፡ ተመልከት ።

** በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ የሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ አስተማሪ ፡ ነበሩ ።

1. እንደ ፡ እንግሊዘኛው ፡ ትርጉም ፡ ከሆነ ፡ የንግድ ፡ ሕጉ ፡ ቁጥር ፡ ፻፵፰ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ "የእንዱስ ትሪ ፡ ንብረት ፡ ባለቤትነት ፡ በልዩ ፡ ሕግ ፡ ይደነገጋል ፡" ይላል ። የአማርኛውና ፡ የፈረንሣይኛው ፡ ትር ጉሞች ፡ ግን ፡ በይበልጥ ፡ አስተካክለው ፡ የሚናገሩት ፡ ስለ ፡ "እንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ ባለቤትነት ፡ ሳይሆን ፡ ስለ ፡ "እንዱስትሪ ፡ ሀብት ፡" ነው ።

2. ኢ.ሔፍ. ጎልድበርግ ፡ "የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ በሕግ ፡ ስለመጠበቅ" ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት፡ ፭ኛ ፡ መጽሔት ፡ በ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ.ም. ፡ ገጽ ፡ ፻፩—፻፳፱ ፡ እና ፡ ከበታች ፡ በሦስተኛው ፡ ክፍል ፡ ስለተፈ ለሰሙ ፡ ጥበቦች ፡ አጠባበቅ ፡ የገለጹትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አስተሳሰቦች ፡ ይመለከቷል ።

3. የዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ትሪቲስ ፡ ኤንድ ፡ አዘር ፡ ኢንተርናሽናል ፡ አክትስ ፡ ተከ ታታይ ፡ እትም ፡ ፪ሺ፰፻፷፬ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ስምምነት ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ የሚመጣው ፡ የመጀመ ሪያው ፡ ችግር ፡ ስምምነቱ ፡ ያለሌላ ፡ ሕግ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ ይችላልን ፡ የሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ነው ።

የሁለቱ ፡ ሀገሮች ፡ ዜጎችና ፡ ኩባንያዎች ፡ አግባብ ፡ ባላቸው ፡ ሕጎች ፡ መሠረት ፡ ምዝገባቸውንና፡ሌሎች ፡ ፎርማሊቲዎችን ፡ አሟልተው ፡ ከቀረቡ ፡ በሌላው ፡ ሀገር ፡ በሚጠቀሙባቸው ፡ የግል ፡ ፍልስማ ፡ ጥበቦች ፡ የንግድ ፡ ምልክቶችና ፡ የንግድ ፡ ስሞች ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ጥበቃ ፡ ይሰጣቸዋል ።[4]

በዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ የዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ዜጎችና ፡ ኩባንያዎች ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የወንጀልና ፡ የፍትሐብሔር ፡ ክስ ፡ እያቀረቡ ፡ (የፍትሐብሔር ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፶፯ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ፻፴፪—፻፴፬ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ፯፻፸፫ ፡ እና ፡ ፯፻፸፬(፭) ፡ ይመለከቷል) ።[5] ደግሞ ፡ በተጨማሪ ፡ ሌሎች ፡ የእንዱስትሪ ፡ ንብረቶችን ፡ መብት ፡ አውቆ ፡ የተላለፈ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ፯፻፸፬(፪) ፡ ስለ"እንዱስትሪ ፡ ንድፎችና ፡ ሥዕሎች ፡ ወይም ፡ በምስክር ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ የተጻፉ ፡ ወይም ፡ ባገር ፡ ደንቦች ፡ ወይም ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነት ፡ በሚገባ ፡ የተጠበቁትንና ፡ የተመዘገቡትን ፡ ከዕውቀት ፡ የመነጨ፡ ጥበቦችን ፡ ወይም ፡ የተመሰከረላቸውን ፡ የሥራ ፡ ዓቅዶች ፡ የተከለከለውን ፡ ሥራ ፡ የሠራባቸው ፡"[6] ይቀጣል ።

የዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ እና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዓለም—አቀፍ ፡ ውል ፡ አንዳንድ ፡ የትርጉም ፡ ችግሮችን ፡ አስከትሏል ። ለምሳሌ ፡ በእንዱስትሪ ፡ በኩል ፡ የተፈለሰሙ ፡ ጥበቦችን ፡ የሚያስከብሩ ፡ ሕጎችን ፡ ባላዘጋጀበትና ፡ ባላወጀበት ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በውሉ ሥር ፡ ያለባትን ፡ ግዴታ ፡ ማለት ፡ ለአሜሪካ ፡ ዜጋዎችና ፡ ኩባንያዎች ፡ "አጥጋቢ ፡ ጥበቃ" ፡ አድርጋለች ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ፡ ወይ ? አንድ ፡ ሰው ፡ አንቀጽ ፡ ፱ ፡ ንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ን ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ሌላ ፡ ሕግ ፡ አያስፈልገውም ፤ ስለዚህም ፡ በፍትሐብሔር ፡ ክስ ፡ ሊከበር ፡ የሚችል ፡ የንብረት ፡ መብት ፡ ያስገኛል ፡ ካላለ ፡ በስተ

---

ይህም ፡ አንቀጽ ፡ ፱ ፡ ንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ፡ ለአሜሪካ ፡ ዜጎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ መብቶችን ፡ ይሰጣቸዋል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መብቶችን ፡ ለመፍጠር ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ሕጎች ፡ ለማወጅ ፡ ተስፋ ፡ ሰጥቷል ፡ ማለት ፡ ነው? ለምሳሌ ፡ ያህል ፤ በተፈለሰመ ፡ ጥበብ ፡ ላይ ፡ አንቀጽ ፡ ፱ ፡ ንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የንብረትነት ፡ መብት ፡ ይሰጣል፤ ማለት ፡ አንድ ፡ የአሜሪካ ፡ ዜጋ ፡ የፈለሰመውን ፡ ጥበብ ፡ በፍትሐብሔርና ፡ በወንጀል ፡ ክስ ፡ ለማስከበር ፡ ይችላልን? የንብረት ፡ መብት ፡ ከሰጠ ፡ ከተሻሻለው ፡ ሕገ—መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ ጋር ፡ ችግር፡ ሊፈጠር ፡ ይችላል ፤ ምክንያቱም ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ "ሞኖፖሊን ፡ የሚመለከቱ ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ውሎችና ፡ እንዲሁም ፡ የዓለም—አቀፍ ፡ ስምምነቶች ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከመጽደቃቸው ፡ በፊት ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ እንዲስማማባቸው ፡ ያዛል ። የእንዱስትሪ ፡ ባለቤትነት ፡ መብቶች ፡ ሞኖፖሊን ፡ ይመለከታሉ ፡ ከተባለ ፡ የተባለው ፡ ችግር ፡ ሊመጣ ፡ ይችላል ። አሁን ፡ የምንነጋገርበት ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ውል ፡ ግን ፡ የፀደቀው ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ—መንግሥት ፡ ከመታወጁ ፡ በፊት ፡ እ.አ.አ. በጥቅምት ፡ ፳ ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ ፓርላማው ፡ እንዲስማማበት ፡ ባይጠየቅም ፡ እንኳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችም ፡ ሆኑ ፡ ተርጓሚዎች ፡ ውሉን፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ማድረግን ፡ ቀጥለዋል ። አበራ ፡ ጀምበሬ ፡ "በኢትዮጵያ ፡ ውል ፡ የመዋዋል ፡ ሥልጣንና ፡ የውል ፡ የበላይ ፡ ሕግነት ፤" የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፪ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ እ.አ.አ.(፲፱፻፷) ገጽ ፫፻፹፩—፬፻፺፪ ፡ ይመለከቷል ። የንብረት ፡ መብት ፡ ካልተፈጠረ ፡ ግን ፡ በዓለም ፡ አቀፍ ፡ ውል ፡ ምክንያት ፡ የሚመጣውን ፡ ግዴታ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ አሟልቷልን?

4. በእዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ሥር ፡ የሚመጡት ፡ የተፈለሰሙ ፡ ጥበቦች ፡ የንግድ ፡ ስሞችና ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ብቻ ፡ መሆናቸውን ያስታውሷል ። እንደንድፎች ፡ እና ፡ እንደሞዴሎች ፡ ያሉት ፡ የሌሎቹ ፡ የእንዱስትሪ ፡ ዓይነቶች ፡ ጥበቃ ፡ በውል ፡ ሰጭውና ፡ በውል ፡ ተቀባይ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ተትተዋል ።

5. አንቀጽ ፡ ፱ ፡ ንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ፡ ያለሌላ ፡ ሕግ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ለመዋል ፡ ይችላል ፡ ከተባለ ፡ አንድ ፡ የአሜሪካ ዜጋ ፡ ወይም ፡ ኩባንያ ፡ በውድድር ፡ ላይ ፡ ሳይሆን ፡ የንግድ ፡ ስሙን ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ምልክቱን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለማስከበር ፡ ይችል ፡ ይሆናል ።

6. "በኖሩት ፡ የዓለም ፡ አቀፍ ፡ ስምምነቶች ፡ የተጠበቀ" ፡ የሚለው ፡ አነጋገር ፡ ችግር ፡ ይፈጥር ፡ ይሆናል። የዓለም—አቀፍ ፡ ውል ፡ ያለሌላ ፡ ሕግ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ለመዋል ፡ አይችልም ፡ ከተባለ ፡ በእንዱስትሪ ፡ በኩል ፡ የሚፈለሰሙ ፡ ጥበቦችን ፡ ይጠብቃል ፡ ለማለት ፡ ይችላልን? ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ውሉ ፡ በእንዱስትሪ፡ በኩል ፡ የተፈለሰሙ ፡ ጥበቦችን ይጠብቃል ፡ ካልተባለ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፸፬

ቀር ፡ "አጥጋቢ ፡ ጥበቃ" ፡[7] የሚለው ፡ ቃል ፡ ጠበቅ ፡ ብሎ ፡ ቢተረጎም ፡ እንኳ ፡ ለአንድ ፡ የተፈለሰመ ፡ ጥበብ ፡ የፍትሐብሔር ፡ መፍትሔ ፡ ስለማይሰጥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አጥጋቢ ፡ ጥበቃ ፡ በሕግ ፡ ለመስጠት ፡ አልቻለም ፡ ሊያሰኝ ፡ ይችላል ። የዩናትይድ ፡ ስቴትስ ፡ መንግሥት ፡ ይህን ፡ ጥያቄ ፡ ባያነሣም ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በግሉ ፡ ይህ ፡ የዓለም—አቀፍ ፡ ውል ፡ የሚያስከትለውን ፡ ግዴታ ፡ በክስ ፡ ለማስከበር ፡ ባይችልም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የሚሻለው ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ ቀስቃሽነትን ፡ ሳይጠብቅ ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ሆነ ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ሰዎችን ፡ የሚጠብቅ ፡ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ሕግ ፡ ማውጣት ፡ ነው ።

ከአንቀጽ ፡ ፱ ፡ ንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ፡ ጋር ፡ ሊነሣ ፡ የሚችለው ፡ ሌላ ፡ ችግር ፡ "ምዝገባንና ፡ ሌሎች ፡ ፎርማሊቲዎችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ሕጎችና ፡ ደንቦች ፡ ካሉ" ፡ የሚለው ፡ ሐረግ ፡ ነው ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ምዝገባን ፡ የሚመለከት ፡ በአግባቡ ፡ መሠረት ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ የላትም ። ሆኖም ፡ የንግድና ፡ እንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ በውስጥ ፡ ደንብ ፡ የሚተዳደሩ ፡ የንግድ ፡ ምልክትና ፡ የእንዱስትሪ ፡ ባለቤትነት ፡ መዛግብት አለው ።[8] አንድ ፡ አሜሪካዊ ፡ የውስጥ ፡ ደንቦቹ ፡ አግባብ ፡ ባለው ፡ ሁኔታ ፡ የወጡ ፡ ሕጎች ፡ አይደሉም ፡ በማለት ፡ እነዚሁ ፡ ሕጎች ፡ የሚያዙትን ፡ ሥነ—ሥርዓት ፡ ሳያሟላ በእንዱስትሪ ፡ በኩል ፡ የፈለሰመውን ፡ አንድ ፡ ጥበብ ፡ ክስ ፡ በማቅረብ ፡ ሊያስከብር ፡ ይችላል ፡ ወይ? የንግድ ፡ ምልክቶችን ፡ በሚመለከት ፡ አንድ ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለንግድ ፡ ምልክቶች ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ፡ "አንዱ ፡ ሰው ፡ መብቱን ፡ ለማስጠበቅ ፡ በጊዜው ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ በመጀመሪያ ፡ ማስመዝገብ ፡ አለበት ።"[9] ስለዚህም ፡ የተሻለ ፡ የሚመስለን ፡ የአሜሪካ ፡ ዜጋዎች ፡ ወይም ፡ ኩባንያዎች ፡ በውስጥ ፡ ደንቦቹ ፡ መሠረት ፡ በንግድና ፡ የእንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ መመዝገባቸው ፡ ነው ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱፻፷፬(፪) ፡ በእንዱስትሪ ፡ በኩል ፡ የተፈለሰሙ ፡ ጥበቦችንና ፡ ሌሎችም ፡ የእንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ መብቶች ፡ እንዲመዘገቡ ፡ ያዛል ።[10]

---

(፪) ፡ አስፈላጊነቱ ፡ ለምንድን ፡ ነው? እዚህ ፡ ለማሳየት ፡ የምንፈልገው ፡ ይህ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱፻፷፬(፪) ፡ እንደ ፡ አንቀጽ ፡ ፱ ፡ ንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ፡ ያሉትን ፡ የዓለም—አቀፍ ፡ ውሎች ፡ ከሥራ ፡ ለማዋል ፡ የወጣ ፡ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ሕግ ፡ መሆኑን ፡ ነው ።

7. ማንም ፡ መንግሥት ፡ ያወጣውን የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ሕግ ፡ የዓለም ፡ ሰላም ፡ እንደሚጠባበቅበት ፡ ነው ፡ እያለ ፡ ስለሚሠጋ ፡ ይህ ፡ ሐረግ ፡ ጠበቅ ፡ ብሎ ፡ መነበብ ፡ አለበት ። ስለዚህ ፡ የሚያዘው ፡ በሕግ ፡ ጥበቃን ፡ ብቻ ፡ የሚለይ ፡ የሥነ—ሥርዓት ፡ ሸክም ፡ እንዳይኖር ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ መተርጎም ፡ አለበት ።

8. ከበታች ፡ በክፍል ፡ አራት ፡ የተገለፀውን ፡ ይመለከቷል ።

9. ከሳሽ ፡ አዛነው ፡ ዓለሜ ፡ ተከሳሽ ፡ ሲንጀር ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ ሃላፊነቱ ፡ የተወሰነ ፡ ኩባንያ ፡ (የፍትሐብሔር ፡ ይግባኝ ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ሺ፪፻፵/፺፮) ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፪ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ (፲፱፻፷፰ ፡ እ.አ.አ.) ፡ ገጽ ፡ ፪፻፲—፪፻፲፱ ። ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስተያየቱ ፡ ጋር ፡ ብንስማማም ፡ ባንስማማም መመዝገብ ፡ ስለባለቤትነትና ፡ ስለምልክቱ ፡ አጠቃቀም ፡ ለሕዝቡ ፡ በማስታወቅ ፡ በኩል ፡ ጠቃሚ ፡ አገልግሎት ፡ አለው ።

10. እላይ ፡ ባለው ፡ ክፍል ፡ የተነገረው ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ በቂ ፡ አይደለም ። የተለዩ ፡ አንዳንድ ፡ ድርጊቶችን ፡ ብንወስድ ፡ ተጨማሪ ፡ ችግሮች ፡ ያጋጥሙናል ። ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ምልክት ፡ ካስመዘገበ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ደግሞ ፡ ተመሳሳይ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የሆነ ፡ ምልክት ፡ በአሜሪካ ፡ ቢያስመዘግብ ፡ ምን ፡ ይሆናል? በትክክል ፡ ባልሆነ ፡ የውድድር ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችለው ፡ ነጋዴው ፡ "እውነተኛ ፡ የንግድ ፡ አሠራር ፡ ተጠቅሟል ፡ ወይስ ፡ አልተጠቀም" (የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፻፴፫(፩)) ፡ የሚለው ፡ ስለሆነ ፡ አስቀድሞ ፡ የተደረገ ፡ ማስመዝገብ ፡ አመልካች ፡ መሆን ፡ የለበትም ። ተመሳሳይ ፡ ከሆኑ ፡ ዕቃዎች ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ በአብዛኛው ፡ የዓለም ፡ ክፍል ፡ ምልክቱ ፡ የታወቀ ፡ ከሆነ ፡ በአሜሪካ ፡ ክስ ፡ የሚያቀርበው ፡ ከሳሽ ፡ የተከሳሹ ፡ ሥራ ፡ ይህን ፡ ጥቂቱን የሞራል ፡ መለኪያ ፡ እንደማያሟላ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማሳየት ፡ ይችላል ።

እንደነዚህ ፡ ካሉት ፡ ችግሮች ፡ በስተቀር ፡ አንቀጽ ፡ ፱(፪) ፡ ግልጽ ፡ ነው ፤ ማለትም ፡ የአሜሪካ ፡ ዜጎች ፡ ወይም ፡ ኩባንያዎች ፡ በአንዳንድ ፡ ሁኔታዎች ፡ በእንዱስትሪ ፡ በኩል ፡ የፈጠሯቸውን ፡ በተለይም ፡ በእንዱስትሪ ፡ በኩል ፡ የፈለሰሟቸውን ፡ ጥበቦች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለማስከበር ፡ ሲችሉ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ግን ፡ የእንዱስትሪ ፡ መብቶች ፡ ልዩ ፡ ሕጎች ፡ ስላላወጡ ፡ ማስከበር ፡ አይችሉም ፡ ማለት ፡ ነው ። በእንዱስትሪ ፡ በኩል ፡ አንድ ፡ ጥበብ ፡ ለመፈልሰም ፡ የሚችሉት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ጥቂት ፡ ስለሆኑ ፡ በዓለም ፡ አቀፍ ፡ ውሎች ፡ በእንዱስትሪ ፡ በኩል ፡ የሚገኙትን ፡ ጥበቦች ፡ በመጠበቅ ፡ ቴክኔዎሎጂ ፡ ወደሀገሬ ፡ እንዲገባ ፡ ለማበረታታት ፡[11] አሁን ፡ ያለውን ፡ አድላዊ ፡ ሁኔታ ፡ (የያንዳንዱን ፡ የዓለም—አቀፍ ፡ ውል ፡ በምክር ፡ ቤቱ ፡ እንዲያልፍ ፡ ማድረጉ ፡ የሚያመጣውን ፡ ችግር ፡ እንኳ ፡ ሳናነሣ) ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የእንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ አዋጅ ፡ እያዘጋጀና ፡ ለፓርላማው ፡ እያቀረበ ፡ የእንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ መብቶች ፡ የሚያስከትለውን ፡ ችግር ፡ እንዲያስወግድ ፡ ሊያበረታታ ፡ ይገባል ። ይኸውም ፡ አዋጅ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሥራውን ፡ ለሚያካሔዱ ፡ ሁሉ ፡ መሥራት ፡ አለበት ።

## ፪. የኤርትራ ፡ ሕግ ።

ኤርትራ ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ በነበረችበት ፡ ጊዜ ፡ የቅኝ ፡ ግዛት ፡ አስተዳዳሪዎችዋ ፡ የንግድ ፡ ምልክትን ፡ የተፈለሰሙ ፡ ጥበቦችን ፡ እና ፡ ንድፎችን ፡ የሚጠብቁ ፡ ሕጎች ፡ አውጀው ፡ ነበር ።[12]

እ.አ.አ. በ፲፱፻፶፪ ፡ በወጣው ፡ የኤርትራ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፺፮ ፡ መሠረት ፡ እነዚህ ፡ የኢጣልያ ፡ ሕጎች ፡ በፌዴሬሽን ፡ ግዛት ፡ ሥር ፡ በሆነችው ፡ በኤርትራ ፡ ላይ ፡ መሥራታቸውን ፡ እንዲቀጥሉ ፡ አድርጓል ።[13] እ.አ.አ. በመጋቢት ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ እንኳ ፡ በኤርትራ ፡ ያለው ፡ የዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ምንም ፡ መሻሻል ፡ ሳያስፈልጋቸው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለመቀጠል ፡ እንደሚችሉ ፡ ተናግሯል ።[14] ባሁኑም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የሚገኘው ፡ የንግድና ፡ የእንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በኢጣልያ ፡ ሕጎች ፡ መሠረት ፡ በንግድ ፡ ምልክትና ፡ በእንዱስትሪ ፡ ባለቤትነት ፡ መዛግብት ፡ ለማስገባት ፡ አዳዲስ ፡ ማመልከቻዎችን ፡ ይቀበላል ።[15]

---

11. የተባበሩት ፡ መንግሥታትን ፡ የኤኮኖሚና ፡ የኅብረ—ሰብ ፡ ጉዳይ ፡ ክፍል ፡ ዘ ፡ ሮል ፡ ኦፍ ፡ ፓተንትስ ፡ ኢን ፡ ዘ ፡ ትራንስፈር ፡ ኦፍ ፡ ቴክኒዎሎጂ ፡ ቱ ፡ ዴቨሎፒኢንግ ፡ ካንትሪይስ ፡ (እ.አ.አ.፡ ፲፱፻፷፬ ፡) እና ፡ ዩናይትድ ፡ ቢሩ ፡ ፎር ፡ ዘ ፡ ፕሮቴክሽን ፡ ኦፍ ፡ ኢንቴሌክችዋል፡ፕሮፐርቲ፡(ቢ.አይ.አርፒ.አይ) ፡ ሞዴል ፡ ሎው ፡ ፎር ፡ ዴቨሎፒኢንግ ፡ ካንትሪይስ ፡ ኦን ፡ ኢንቬንሽንስ ፡ (እ.አ.አ. ፡ ፲፱፻፷፭) ፡ ገጽ ፡ ፲፯ ፡ ይመለከቷል ።
12. በኤ.ሞሪ ፡ የታተመ ፡ ማንዋል ፡ ዲ ፡ ሊጅላዚዮን ፡ ዴላ ፡ ኮሎንያ ፡ ኤርትሪያ ፡ ፪ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ (በ፲፱፻፲፬ ፡ እ.አ.አ.) ፡ ገጽ ፡ ፪፵—፪፵፯ ።
13. አንቀጽ ፡ ፺፯(፩) ፡ "በሚያዝያ ፡ ፲፱፻፵፩ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የነበሩት ፡ ሕጎችና ፡ ደንቦች ፡ እንዲሁም ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚያውላቸው ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ካልሻሯቸው ፡ ... ያልተሻሩትና ፡ ያልተሻሻሉት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ ይቀጥላሉ ፡" ይላል ። ሕገ—መንግሥቱን ፡ የኤርትራው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ እ.አ.አ. ሐምሌ ፡ ፲ ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ተቀብሎታል ፤ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትም ፡ እ.አ.አ. ነሐሴ ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ አጽድቀውታል ።
14. በኤርትራው ፡ የጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ እ.አ.አ. በመጋቢት ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ የተዘጋጀ ፡ ማስታወሻ ፡ (ያልታተመ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጥናት ፡ እንስቲትዩት ፡ አ.አ.)
15. ከአቶ ፡ ዮሐንስ ፡ ብርሃኔ ፡ የአሥመራው ፡ የንግድ ፡ የእንዱስትሪና ፡ ቱሪዝም ፡ ሚኒስቴር ፡ ቅርንጫፍ ፡ አጠቃላይ ፡ ዲሬክተር ፡ ጋር ፡ እ.አ.አ. በየካቲት ፡ ፩ ፡ ፲፱፻፸፩ ፡ የተደረገ ፡ መጠይቅ ።

የኤርትራን ፡ በፌዴሬሽን ፡ መተዳደር ፡ ያስቀረው ፡ ትዕዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፯ ፡ እ.አ.አ በ፲፱፻፶፭[16] ከወጣ ፡ ወዲህ ፡ ግን ፡ የነዚህ ፡ ሕጎች ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ መዋል ፡ በተለይም ፡ ለመመዝገብ ፡ የሚጸፋትን ፡ ማመልከቻዎች ፡ መሻር ፡ አለመሻር ፡ አጠራጣሪ ፡ ሆኗል ። የነዚህ ፡ ሕጎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋል ፡ መቻላቸው ፡ አጠራጣሪ ፡ ከሆነ ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ አስመዝጋቢዎቹ ፡ ለማግኘት ፡ የሚሹት ፡ የተፈለሰሙ ፡ ጥበቦች ፡ መጠበቅ ፡ ፈርሰዋል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ትዕዛዙ ፡ በ፲፱፻፶፭ ፡ ሲወጣ ፡ የነበረው ፡ የሕጎቹ ፡ መፍረስና ፡ ያለመፍረስ ፡ ጥርጣሬ ፡ የተፈጠረው ፡ ከትዕዛዙ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ፡ ላይ ፡ ለመመሥረት ፡ በሚችሉት ፡ የተለያዩ ፡ አተረጓገሞች ፡ ነው ።[17] አንቀጽ ፡ ፪ ፡ "እስካሁን ፡ የነበረው ፡ አስተዳደር ፡ እንዲቀጥል ፡ የሚያስፈልግ ፡ ከሆነ" ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የነበሩት ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ ተለይተው እስኪሻሩ ፡ ድረስ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ይውላሉ ፡ ይላል ። ባንድ ፡ በኩል ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ የኤርትራ ፡ ሕጎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ ለመቀጠል ፡ የሚችሉት ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛቱ፡ የግል ፡ አስተዳደር ፡ አስተዳደሩ ፡ እንዳይፈርስ ፡ ለማድረግ ፡ ወይም ፡ በትዕዛዙ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ እና ፡ ፭ ፡ የተሰጡትን ፡ መብቶች ፡ ለመጠበቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለመከራከር ፡ ይቻላል ።[18] በሌላ ፡ አነጋገር ፡ ትዕዛዙን ፡ በጠቅላላ ፡ ስንመለከት ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ፡ የወጣው ፡ ሁሉም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ተወላጆች ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ ሕግ ፡ እንዲተዳደሩ ፡ በማሰብ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የሆነ ፡ አጠቃላይ ፡ ሕግ ፡ ለመመሥረት ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። በሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የትዕዛዙ ፡ ዓላማ ፡ አንድ ዓይነት ፡ የሆነ ፡ አጠቃላይ ፡ ሕግ ፡ በሀገሪቷ ፡ ለመፍጠር ፡ ሳይሆን ፡ በፌዴሬሽኑ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ አንዳንድ ፡ የአስተዳደር ፡ ውዝግቦች ፡ ለማስወገድ ፡ ነው ፤ ማለትም ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ ፭ ፡ እና ፡ ፪ ፡ የወጡት ፡ የትዕዛዙ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋል ፡ የተሰጡትን ፡ መብቶች ፡ ሆነ ፡ እንዲሁም ፡ የነበሩትን ፡ ሕጎች ፡ እንዳያደናቅፍ ፡ ለማድረግ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መከራከር ፡ ይቻላል ።[19]

16. የኤርትራ ፡ በፌዴሬሽን ፡ መተዳደር ፡ መቅረትና ፡ የኤርትራ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋር ፡ በአንድ ፡ ሕግ ፡ ሥር ፡ የመተዳደር ፡ ትዕዛዝ ፡ እ.አ.አ. ፲፱፻፶፭ ፡ ቁጥር ፡ ፳፯ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፪ኛው ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፫።

17. ለተባለው ፡ አግባብነት ፡ ያለው ፡ የቁጥር ፡ ፪ ፡ ክፍል ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ "የታወጁ ፡ ውሳኔዎች ፡ ሕጎችና ፡ ደንቦች ፡ ወይም ፡ የነዚሁ ፡ አንዳንድ ፡ ክፍሎች ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በኤርትራ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የዋሉ ፡ ከሆነ ፡ ... እስካሁን የነበረውን ፡ አስተዳደር ፡ ማስቀጠል ፡ አስፈላጊ ፡ እስከሆኑ ፡ ድረስ ፡ ወደፊት ፡ በሚመጡ ፡ ሕጎች ፡ በግልጽ ፡ እስኪተኩ ፡ ድረስ ፡ በሙሉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ይቀጥላሉ ። እንዲሁም ፡ እነዚህን ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ሲያውል ፡ የነበረው ፡ አስተዳደር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ ሥራውን ፡ ይቀጥላል ።"
ለተለያዩ ፡ አተረጓጎሞች ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ አር.ሚ.ሜንስ ፡ "እ.አ.አ. የ፲፱፻፶፯ ፡ የኤርትራ ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ያለው ፡ አቋም" ፤ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፭ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ (፲፱፻፷፭ ፡ እ.አ.አ.) ፡ ገጽ ፡ ፪፻፸፫—፪፻፹፪ ፡ በገጽ ፡ ፪፻፸፯—፪፻፸፯ ፡ ላይ ፤ ፺ ፡ ቫንደርሊንደን ፡ ኢንትሮደክሲዮን ፡ ኡ ፡ ድዋ ፡ ሊትዮፒ ፡ ሞዴርን ፡ (፲፱፻፷፩ ፡ እ.አ.አ.) ፡ ገጽ ፡ ፪—፰.

18. ትእዛዙ ፡ እስከ ፡ ወጣበት ፡ ማለት ፡ እስከ ፡ እ.አ.አ. ህዳር ፡ ፲፭ ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ድረስ ፡ በኢጣሊያዊያን ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የተሰጡ ፡ የእንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ መብቶች ፡ በትዕዛዙ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ የተጠበቁ ፡ መብቶች ፡ ስለሆኑ ፡ በኤርትራ ፡ የንግድ ፤ የእንዱስትሪና ፡ ቱሪዝም ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ("በሥራ፡ላይ ፡ የቆየው ፡ አስተዳደር") ፡ የእንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ መዝገቦችን ፡ እንዳሉ ፡ ማቆየት ፡ አለበት ። እንዲሁም፡ ሕጎቹ ፡ የምዝገባውን ፡ አሠራርና ፡ በመመዝገብ ፡ የሚገኙትን ፡ መብቶች ማስከበር ፡ መቀጠል ፡ አለባቸው ። አዲስ ፡ ማመልከቻዎችን ፡ መመዝገብ ፡ ግን ፡ ለመዝገቡ ፡ መቀጠል ፡ አስፈላጊ ፡ ስላልሆኑ ፡ ከላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ አተረጓጎሞች ፡ መሠረት ፡ መቅረት ፡ አለባቸው ።

19. አዋጆችን ፡ በሚያውጁበት ፡ ጊዜ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከፓርላማው ፡ ጋር ፡ እንዲሠሩ፡ሕገ—መንግሥቱ ፡ ያዛል ። ስለዚህም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አዋጆችን ፡ ወደ ፡ ፓርላማ ፡ በማይሄደው ፡ በትዕዛዙ ፡ እንዲሽራቸው ፡ መፍቀድ ፡ በሕገ—መንግሥቱ ፡ አንቀጽ፡ ፹፯—፺፩ ፡ የተነገሩትን ፡ የሕግ ፡ እወጃ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቶች ፡ ማቃለል ፡ ይሆናል ። ይህ ፡ አተረጓጎም ፡ በሕገ—መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፹፯ ፡ ስለተሰጠው ፡ የመ

አንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለኤርትራ ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ ሕግ ፡ በሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ የፖለቲካ ፡ ጥያቄዎችንም ፡ ስለማይዘነጋ ፡ (እነዚህም ፡ ጥያቄዎች ፡ ሕጐቹን ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ከማዋል ፡ ይልቅ ፡ የሚያደናቅፉ ፡ ይመስላሉ ፡)[20] በንግድና ፡ በኢንዱስትሪ ፡ ሥራዎች ፡ የተሠማሩ ፡ ሰዎች ፡ ከዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ምን ፡ ብሎ ፡ እንደሚፈርዱ ፡ ለመገመት ፡ ከማያስችለው ፡ አጠራጣሪ ፡ ሁኔታ ፡ ይልቅ ፡ በሕግ ፡ መተዳደርን ፡ ይመርጣሉ ። አሁን ፡ ባለው ፡ አጠራርሪ ፡ ሁኔታ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ይዞታ ፡ ለአንድ ፡ የእንዱስትሪ ፡ ጥበብ ፡ ፈልሳሚ ፡ የሚደረግለት ፡ ጥበቃ ፡ አጥጋቢ ፡ አይደለም ። ይህንን ፡ ችግር ፡ በሚገባ ፡ ለማስወገድ ፡ ከተፈለገ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ በፊት ፡ የነበሩትን ፡ ሕጎች ፡ እየለየ ፡ ውድቅ ፡ በማድረግ ፡ ለጠቅላላ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግዛት ፡ የሚሠራ ፡ የእንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ ሕግ ፡ ማውጣት ፡ አለበት ።

## ፫. በእንዱስትሪ ፡ የተፈለሰሙ ፡ ጥበቦችን ፡ የሚያስከብሩ ፡ ሌሎች ፡ አስተሳሰቦች ፤

አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ የእንዱስትሪ ፡ ጥበቦችን ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ በማስመዝገብ ፡ ወይም ፡ ባለም—አቀፍ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ መብት ፡ ያገኙ ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ዜጎች ፡ በመሆን ፡ ለማስከበር ፡ ሲችሉ ፡ የንግድ ፡ ስሞችንና ፡ የንግድ ፡ ምልክቶችን ፡ ግን ፡ አግባብ ፡ የሌለው ፡ ውድድር ፡ ክስ ፡ በማቅረብ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ መብቱን ፡ ለማስከበር ፡ ይችላል ።[21] ፈልሳሚዎች ፡ ወይም ፡ የእንዱስትሪ ፡ ፕላን ፡ ነዳፊዎች ፡ እስካሁን ፡ መብታቸውን ፡ ማስከበሪያ ፡ የላቸውም ። ሆኖም ፡ ቀጥሎ ፡ እንደምናመለክተው ፡ እነዚሁ ፡ ሰዎች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ መብታችንን ፡ አስጠብቁልን ፡ ብለው፡ ሊጠይቁባቸው ፡ የሚያስችላቸው ፡ አንዳንድ ፡ አስተሳሰቦች ፡ አሉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የነዚህ ፡ አስተሳሰቦች ፡ በቂ ፡ አለመሆን ፡ ለሀገሪቱ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ የእንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ ሕግ ፡ ማስፈለጉን ፡ ያስረዳል ።

### ሀ. አግባብ ፡ የሌለው ፡ ውድድር ፤

አበበ ፡ የሚባለው ፡ ነጋዴ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ይፈለስማል ። ከሱ ፡ ጋር ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሆነው ፡ ነጋዴ ፡ በቀለ ፡ ሳይከፍል ፡ ወይም ፡ አበበ ፡ ሳይፈቅድለት ፡ በተፈለሰመው ፡ ነገር ፡ ይጠቀማል ፡ እንበል ። በንግድ ፡ ሕግ ፡ ፻፴፫ ፡ መሠረት ፡ የበቀለ ፡ ዕቃ ፡ መሸጥ ፡ ወይም ፡ የተፈለሰመውን ፡ ጥበብ ፡ በመጠቀም ፡ አገልግሎት ፡ መስጠት ፡ "እውነተኛ ፡

---

ንግሥቱን ፡ እስተዳደር ፡ በሚወስን ፡ ሥልጣን ፡ የኤርትራን ፡ በፌዴሬሽን ፡ መተዳደር ፡ ለማስቀረት ፡ ያለውን ፡ ሥልጣን ፡ በተለይ ፡ ለመመርመር ፡ ወይም ፡ ቁም ፡ ነገሩ ፡ ስለአንድ ፡ ዓይነት ፡ ሕግ ፡ አወጣጥ ፡ ሳይሆን ፡ ስለአንድ፡ዓይነት ፡ አስተዳደር ፡ ነው ።

የአሥመራው ፡ ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በከሳሽ ሶቼታ ፡ ናስዮናል ፡ ትራንስፖርት ፡ ጓንድራንድ ፡ ወንድማማቾች ፡ እና ፡ በመልስ ፡ ሰጭ ፡ አቶ ፡ ሥዮም ፡ ምስግና ፤ (የፍትሐብሔር ፡ ይግባኝ፡ ቁጥር፡፲፰/፶፰) ፤ የኢትዮጵያ የሕግ ፡ መጽሔት ፤ ፬ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ (፲፱፻፷፯ ፡ እ.አ.አ.) ፡ ገጽ ፡ ፪፻፹፰—፪፻፺፪ ፤ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ይህንን ፡ ሁለተኛ ፡ አስተያየት ፡ የትዕዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፯ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ በመተርጎም ፡ በተጨማሪ ፡ ይደግፋል ። በዚህ ፡ ክስ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩ ፡ ምክንያት ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ሰዎች ፡ በማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ ባለንብረት ፡ ሊሆኑ ፡ አይችሉም ፡ የሚለው ፡ የፍትሐብሔሩ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፲ ፡ በኤርትራ ፡ ለሚገኙ ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ሰዎች ፡ አይሠራም ፡ ሲል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወስኗል ። ሆኖም ፡ ይህ ፡ አተረጓጎም ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ ስለማናቸውም ፡ ንብረት ስለሚናገር ተብሎ ፡ ሊለይ ፡ ይችላል ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ "ማንኛውም ፡ መብት ፡ ሁሉንም ፡ ዓይነት ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ መሆንና ፡ማዘዝም፡ መብቶች ፡ ጨምሮ ፡ ... በሙሉ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ መሆኑን ፡ ይቀጥላል" ፡ ስለሚል ፡ ነው ።

20\. ይህ ፡ ከላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ሚንስን ፡ ገጽ ፡ ፪፰ ፡ እና ፡ ቫንደርሊንደንን፣ ገጽ ፡ ፰ ፡ ላይ ፡ ተነግሮአል ።

21\. የንግድ፡ ምልክትን ፡ አግባብ ፡ በሌለው ፡ ውድድር ፡ ክስ ፡ ስለማስከበር ፡ ከላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስረጃ ፣ ቁጥር ፡ ፪ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ጎልድበርግን ፡ ይመለከቷል ።

ለሆነ ፣ የንግድ ፣ አሠራር ፣ ተቃዋሚ ፣ ነው” ፡[22] በማለት ፣ አበበ ፣ ክስ ፣ አቅርቦ ፣ ከበቀለ ፣ ካሣ ፣ ሊቀበል ፣ ይችላል ።

ሆኖም ፣ አግባብ ፣ የሌለው ፣ ውድድር ፣ ነው ፣ ተብሎ ፣ የሚቀርበው ፣ ክስ ፣ በውድድር ፣ ላይ ፣ ያሉትን ፣ ሰዎች ፣ አንዱን ፣ ከሌላው ፣ ብቻ ፣ ስለሚጠብቅ ፣ በቂ ፣ አይሆንም ፣ ፈልሳሚው ፣ ነጋዴ ፣ ካልሆነ ፣ በውድድር ፣ ላይ ፣ ሊገኝ ፣ አይችልም ፣ ያንዱን ፣ ሰው ፣ ጥበብ ፣ የወሰደ ፣ ጥበቡን ፣ ዕቃ ፣ ለመሥሪያ ፣ ካልተጠቀመበት ፣ ወይም ፣ አንድ ፣ አገልግሎት ፣ መስጫ ፣ ካላደረገው ፣ ውድድር ፣ ውስጥ ፣ ሊገባ ፣ አይችልም ። አንድ ፣ የውጭ ፣ ሀገር ፣ የእንዱስትሪ ፣ ንብረት ፣ መብት ፣ ያለው ፣ ወይም ፣ የፈለሰመ ፣ ሰው ፣ በዚሁ ፣ በተፈለሰመው ፣ ጥበብ ፣ የተሰሩትን ፣ ዕቃዎች ፣ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ካላስገባ ፣ ወይም ፣ የተፈለሰመውን ፣ ጥበብ ፣ በኢትዮጵያ ፣ ውስጥ ፣ ካልተጠቀመበት ፣ የተፈለሰመውን ፣ ጥበብ ፣ ሊወስዱ ፣ ከሚችሉ ፣ በሀገሩ ፣ ውስጥ ፣ ከሚሠሩት ፣ ነጋዴዎች ፣ ጋር ፣ አይወዳደርም ። ይህ ፣ የሚያስከትለው ፣ ውጤት ፣ ፈልሳሚው ፣ የሚጠቀመው ፣ በተጨማሪ ፣ በኢትዮጵያ ፣ ውስጥ ፣ ነጋዴ ፣ የሆነ ፣ እንደሆነ ፣ ነው ። ነጋዴ ፣ ካልሆነ ፣ ግን ፣ ይህን ፣ የፍልሰማ ፣ ካሣ ፣ አያገኝም ፣ ማለት ፣ ነው ። ሆኖም ፣ ዓላማው ፣ መፈልሰምን ፣ ለማበረታታት ፣ ከሆነ ፣ የተደረገው ፣ ልዩነት ፣ እስከዚህም ፣ አጥጋቢ ፣ አይሆንም ።

ያም ፣ ሆነ ፣ ይህ ፣ አግባብ ፣ በሌለው ፣ ውድድር ፣ ላይ ፣ የተመሠረተ ፣ ክስ ፣ ያላግባብ ፣ የሚደረገውን ፣ ውድድር ፣ ለማገድ ፣ የሚወሰድ ፣ እርምጃ ፣ ብቻ ፣ ነው ። ያላግባብ ፣ ውድድር ፣ ክስ ፣ ጠባብ ፣ የሆነበት ፣ ምክንያት ፣ በነጋዴዎች ፣ መካከል ፣ ታማኝነትን ፣ የመፍጠር ፣ ግብ ፣ ፈልሳሚነትን ፣ ለመሸለምና ፣ ለማበረታታት ፣ የሚያስፈልገውን ፣ ጥብቅ ፣ ደንብ ፣ ስለማይጠይቅ ፣ ነው ። ይኸውም ፣ ባንድ ፣ በኩል ፣ የንብረት ፣ መብት ፣ ሞኖፖሊ ፣ እየሰጡ ፣ ምርምርን ፣ (ሪሰርችን) ፣ በማበረታታት ፣ የሚገኘውን ፣ ጥቅም ፣ በመመልከት ፣ ሲሆን ፣ በሌላ ፣ በኩል ፣ ደግሞ ፣ አዲስ ፣ ዘዴዎችንና ፣ ትምህርቶችን ፣ በማራባት ፣ የእንዱስትሪ ፣ ዕድገት ፣ እንዳይደክም ፣ በማድረግ ፣ ሁለቱን ፣ ተመዛዛኝ ፣ ሃሳቦች ፣ ለማስማማት ፣ ነው ።

### ለ. በአዕምሮ ፣ ታስቦ ፣የሚወጣ፣ሥራ ።

የፍትሐብሔር ፣ አንቀጽ ፣ ፲፩ ፣ “የሥራው ፣ ማናቸውም ፣ የአገላለጽ ፣ ዓይነት ፣ መልክ ፣ ፎርም ፣ ማንኛውም ፣ ምስጋና ፣ ወይም ፣ ግብ ፣ ቢኖረው ፣ ” (ቁጥር ፣ ፲፮፻፵፯ (፪) ) ፣ ለሠሪው ፣ በአዕምሮ ፣ ምርምር ፣ ባወጣው ፣ ሥራ ፣ ላይ ፣ ግዙፍነት ፣ የሌለውን ፣ የባለሀብትነት ፣ መብት ፣ ይሰጠዋል ፣ (ቁጥር ፣ ፲፮፻፵፯(፩) ) ። ከነዚሁ ፣ የአዕምሮ ፣ ሥራ ፣ ከሚባሉት ፣ ሁሉም ፣ አጠቃላይ ፣ የሆነው“በሠሪያቸው ፣ አዕምሮ ፣ የተፈጠሩና፣ የዚሁኑ ፣ አሠራር ፣ ልዩነት ፣ የሚያሳዩ ፣ ሎሌችም ፣ ሥራዎች ፣ ሁሉ ፣ናቸው”፣ የሚለው ፣ የፍትሐብሔሩ ፣ አንቀጽ ፣ ፲፩ ፣ ቁጥር ፣ ፲፮፻፵፰(መ) ፣ ነው ። የነዚህ ፣ ሐረጎች ፣

---

22. ይህን ፣ ክስ ፣ በማሸነፍ ፣ የእንዱስትሪ ፣ ንብረት ፣ መብት ፣ ሊፈጠር ፣ ባይቻልም ፣ እንኳ ፣ ተመሳሳይ ፣ የሆኑ ፣ ውጤቶችን ፣ ማስገኘት ፣ ይቻላል ። ለምሳሌ ፣ ምልክቱን ፣ በመጀመሪያ ፣ የተጠቀመበት ፣ እኔ ፣ ነኝ ፣ በሚል ፣ ምክንያት ፣ በነጋዴ ፣ በቀለ ፣ ላይ ፣ ክስ ፣ ሊያቀርብ ፣ ይችል ፣ የነበረው ፣ ነጋዴ ፣ አበበ ፣ ንግዱን ፣ የተፈለሰመውን ፣ አብሮ ፣ ለቸርነት ፣ አስተላለፈ ፣ (ምንም ፣ እንኳ ፣ ከበቀለ ፣ በኋላ ፣ የተፈለሰመውን ፣ ጥበብ ፣ በግል ፣ መጠቀም ፣ ቢጀምርም) ፣ ቸርነት ፣ ከበቀለ ፣ በኋላ ፣ የተፈለሰመውን ፣ ለመጠቀም ፣ አንድ ፣ ዓይነት ፣ የመከሰስ ፣ መብት ፣ እንዲኖረው ፣ ያስፈልጋል ። ይህም ፣ መሆን ፣ ያለበት ፣ ምክንያት ፣ ምንም ፣ እንኳ ፣ ጉዳዩ ፣ ከአበበ ፣ ቁጥጥር ፣ ውጭ ፣ ቢሆን ፣ የተፈለሰመውን ፣ በአሁኑ ፣ ጊዜ ፣ ማንም ፣ ቢጠቀምበት ፣ የበቀለ ፣ ሥራዎች ፣ እውነተኛ ፣ ስላልሆኑ ፣ ነው ። እንደዚህ ፣ ከሆነ ፣ ቸርነት፣ ለሚፈለሰመው ፣ ሥራ ፣ ለአበበ ፣ ለመክፈል ፣ ፈቃደኛ ፣ ይሆናል ፣ ማለት ፣ ነው ።

አነጋገር ፡ ሠፊ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በእንዱስትሪ ፡ በኩል ፡ የፈለሰማ ቸውን ፡ ጥበቦች ፡ በአንቀጽ ፡ ፲፩ ፡ መሠረት ፡ ሊጠበቁ ፡ ይችላሉ ፡ ብሎ ፡ ለመከራከር ፡ ይችላል ።

እንደዚህ ፡ ያለው ፡ አስተያየት ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ተቃውሞዎች ፡ ሊቀርቡበት ፡ ይች ላል ። በንግድ ፡ ሕጉ ፡ በእንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ መካከልና ፡ በሥነ—ጽሑፍና ፡ በኪነ ፡ ጥበብ ፡ ንብረቶች ፡ ልዩነት ፡ እንዳለ ፡ ይገልጻል ። ስለ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍና ፡ ስለኪነ—ጥበብ ፡ ንብረቶች ፡ የንግድ ፡ ሕጉ ፡ ቁጥር ፡ ፻፵፱(፪) ፡ አርእስቱ ፡ "የሥነ—ጽሑፍና ፡ የኪነ ፡ ጥበብ ፡ ባለሀብትነት" ፡ ወደተሰኘው ፡ ፍትሐብሔር ፡ አንቀጽ ፡ ፲፩ ፡ ይመራል ። ስለ ፡ እንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ ደግሞ ፡ ቁጥር ፡ ፻፵፰(፪) ፡ ወደ ፡ "ልዩ ፡ ሕጎች" ፡ ይመራል ። የዚህ ፡ ትርጉም ፡ ግልጽ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ልዩ ፡ ሕጎች ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይወጣሉ ፡ ማለት ፡ ሲሆን ፡ የንግድ ፡ ሕጉ ፡ በሚወጣበት ፡ ጊዜ ፡ አብረው ፡ የታወጁት ፡ የፍት ሐብሔሩ ፡ ቁጥሮች ፡ በእንዱስትሪ ፡ በኩል ፡ ለተፈለሰሙ ፡ ጥበቦች ፡ ጥበቃን ፡ ይሰጡ ዘንድ ፡ ታስበው ፡ አልወጡም ፡ ማለት ፡ ነው ።

በተጨማሪም ፡ የፍትሐብሔሩ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፩ ፡ በእንዱስትሪ ፡ በኩል ፡ የሚፈለ ሰሙ ፡ ጥበቦችንም ፡ ይጨምራል ፡ ከተባለ ፡ ያለመመዝገብ ፡ ያለማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሳይመረምሩት ፡ አንድ ፡ በእንዱስትሪ ፡ የተፈለሰመ ፡ ጥበብ ፡ "ከታተመበት" ፡ (ማለት ፡ ለሕዝቡ ፡ ከተገለፀበት) ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ቢያንስ ፡ ለ፶ ፡ ዓመት ፡ ጥበቃን ፡ ያገኛል ፡ ማለት ፡ ነው ።[23] ይህ ፡ አባባል ፡ በእንዱስትሪ ፡ ንብ ረት ፡ በኩል ፡ የኖረውን ፡ ሕግ ፡ ማለትም ፡ ምርምርን ፡ እያበረታቱ ፡ የተፈለሰሙ ፡ ጥበቦ ችን ፡ በሰፊው ፡ ከጥቅም ፡ ላይ ፡ እንዲውሉ ፡ ለማድረግ ፡ የነበረውን ፡ ጥረት ፡ ዋጋ ፡ ያሳ ጣዋል ። ሌላው ፡ ቢቀር ፡ እንኳ ፡ የ፶ ፡ ዓመቱን ፡ የሞኖፖሊ ፡ ጊዜ ፡ የሚወስን ፡ ሕግ ፡ ያስፈልጋል ።[24]

### ሐ. <u>የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሥልጣን</u>፤

የሕዝቡን ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ ደህንነት ፡ ይጠብቃል ፡ በማለት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ባንዳንድ ፡ የንግድ ፡ ክፍሎች ፡ ላይ ፡ ለሰዎች ፡ ሞኖፖሊ ፡ እንደሚሰጡ ፡ ይነገራል ።[25] ይህ ፡ ልገሣ ፡ በየትኛው ፡ የሕገ—መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ሥልጣን ፡ እንደተደረገ ፡ ባይ ገለጽም ፡ ምናልባት ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፴፮ ፡ መሠረት ፡ የተፈጸመ ፡ ነው ፡ ይባል ፡ ይሆናል ።[26] የተሻሻለው ፡ ሕገ—መንግሥት ፡ እ.አ.አ. በ፲፱፻፶፭ ፡ ከመታወጁ በፊት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ያለምንም ፡ ተቃውሞ ፡ የሞኖፖሊ ፡ መስጠት ፡ የበ

---

23. የፍትሐብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ፲፯፻፶፫ ፡ እና ፡ ፲፯፻፸ ።

24. በዓለም ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ለእንዱስትሪ ፡ ፈልሳሚዎች ፡ የሚሰጠው ፡ ጥበቃ ፡ ለ፲፰ ፡ ዓመት ፡ ነው ። ቢ.አይ.አር.ፒ.አይ ፡ ከላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ቁጥር ፡ ፲፩ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ገጽ ፡ ፵፰ ፡ ይመለከቷል ።

25. ከሁሉም ፡ የላቀው ፡ ስለተፈለሰመው ፡ የአገሪቱ ፡ <u>የእንጀራ</u> ፡ መጋገሪያ ፡ በቅርብ ፡ የነበረው ፡ ክርክር ፡ ነው ። ከተከራካሪዎቹ ፡ አንደኛው ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ስለፈቀዱልኝ ፡ የአምስት ፡ አመት ፡ ሞኖፖሊ ፡ ይገባኛል ፡ ባይ ፡ ነው ። አሁን ፡ ክሱ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይገኛል ።

26. ተፈላጊ ፡ የሆነው ፡ የአንቀጽ ፡ ፴፮ ፡ ክፍል ፡ "ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የበላይ ፡ ገዥ ፡ በመሆኑ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ... የነዋሪዎቹንም ፡ ጥቅምና ፡ ደህንነት ፡ ... በዚህ ፡ ሕገ—መንግሥት ፡ የተጻፉት ፡ ቃሎች ፡ ሳይጎድሉ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የተገለጹትን ፡ ተግባሮች ፡ ሁሉ ፡ ለማስፈፀም ፡ የሚያስፈልጉት ፡ መብቶችና ፡ ሥልጣኖች ፡ አሉት ፡" ይላል ። በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ላይ ፡ ስለተሰጡት ፡ የተለያዩ ፡ አተረጓጎሞች ፡ ጄ.ሲ.ኤን. ፓል ፡ እና ፡ ክላፈም ፡ <u>ኢትዮጵያን ፡ ኮንስቲትዩሽናል ፡ ዴቬሎፕ ሜንት</u> ፡ ፪ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ (፲፱፻፷፯ ፡ እ.አ.አ.) ፡ ገጽ ፡ ፬፻፷፩—፬፻፷፪ ፡ ይመለከቷል ።

ላይነት ፡ ሥልጣን ፡ ነበራቸው ።[27] የሀገሪቷን ፡ የኢንዱስትሪ ፡ እድገት ፡ ወይም ፡ ለሕዝቡ ፡ ጤንነት ፡ የሚጠቅመውን ፡ ነገር ፡ ለፈለሰመ ፡ ሰው ፡ መሸለም ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ ሥልጣን ፡ ውጭ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ። በሠፊው ፡ ሲነበብ ፡ አንቀጽ ፡ ፴፮ ፡ የሚናገረው ፡ በሕገ—መንግሥቱ ፡ ሌሎች ፡ አንቀጾች ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከተሰጡት ፡ ሥልጣኖች ፡ ውጭ ፡ ስላሉት ፡ ቀሪ፡ሥልጣኖች ፡ ነው።በተጨማሪም ፡ ሕገ—መንግሥቱ ፡ በሚለው ፡ አሠራር ፡ መሠረት ፡ ሕጎቹ ፡ እስኪሻሻሉ ፡ ድረስ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ያወጇአቸው ፡ ሕጎች ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ቀሪ ፡ ሥልጣኖች፡አግኝተው ፡ ይይዙ ፡ ይሆናል ።

እንደ ሕገ—መንግሥቱ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ አንቀጽ ፡ ፵፯፡ምናልባት ፡ ንጉሠ ነገሥቱ ፡ ሞኖፖሊ ፡ እንዲሰጥ ፡ የታሰበ ፡ አይደለም ። አንቀጽ ፡ ፵፯ ፡ "ማንኛውም ፡ የኢትዮጵያ ዜጋ ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ ማናቸውንም ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ እየሠራ ፡ ለመኖር ፡ ...መብት ፡ አለው" ይላል ። ይህን ፡ መሠረታዊ የሆነ ፡ ሕገ—መንግሥታዊ ፡ መብት ፡ ሊቀንስ ፡ የሚችል ፡ "ሕግ" ፡ ብቻ ፡ ነው ። በሕገ—መንግሥቱ ፡ መሠረት ፡ መብትን ፡ ሊቀንስ ፡ ከተፈለገ ፡ በአንቀጽ ፡ ፷፭ ፡ መሠረት ፡ መሆን ፡ አለበት ። ማስታወቂያ ፡ ሳይወጣ ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ የሚደረግ ፡ የተለየ ፡ ስጦታ ፡ አሁን ፡ እንደምንነጋገርበት ፡ ዓይነት ፡ "ሕግ" ፡ ሊቆጠር ፡ አይችልም ። እንዲሁም ፡ በንግድ ፡ ሕጉ ፡ ቁጥር ፡ ፳፪ ፡ እና ፡ ፳፫ ፡ መሠረት ፡ "ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ስለንግድ ፡ በወጡት ፡ ሕጋዊ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ያሉበትን ፡ ግዴታዎችን፡ እየፈፀመ" ፡ እና ፡ "በሕግ ፡ የተከለከሉ ፡ ወይም ፡ የተወሰኑ ፡ ነገሮችን፡"እየተመለከተ ፡ ማንኛውንም ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ መብት ፡ አለው ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከፓርላማው ፡ ጋር ፡ ይህ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የተሰጠ ፡ የመነገድ ፡ መብት ፡ መኖሩን ፡ አረጋግጠዋል ። ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የሚደረጉ ፡ የዚህ ፡ መብት ፡ ቅነሳ ፡ ውሳኔዎች ፡ ንጉሠ፡ነገሥቱ ፡ እና ፡ ፓርላማው ፡ በተስማሙበት ፡ ሕጎች ፡ መሠረት ፡ ብቻ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ።

እስካሁን ፡ ያየናቸው ፡ አስተያየቶች ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከታወጀ ፡ ወዲህ ፡ ንጉሠ፡ ነገሥቱ ፡ ላንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ በሰጡት ፡ የተወሰኑ ፡ ሞኖፖሊዎች ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ አጥጋቢ ፡ መሆናቸው ፡ ጥርጣሬን ፡ ያሳድራል ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሞኖፖሊን ፡ መስጠቱ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ጥቅምና ፡ ደህንነት ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ማመናቸውንና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ መብቶችን ፡ የሚያስከብር ፡ አዋጅ ፡ ማስፈለጉን ፡ ያመለክታል ።

## መ. የፈቃድ ፡ (የሌቸንሳ) ፡ ሕግ ፤

አንድ ፡ ሰው ፡ ንግድ ፡ ወይም ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሥራ ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ የመንግሥት ፡ ፈቃድን ፡ እንዲያገኝ ፡ የሚያዙት ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የወጡት ፡ የንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ፈቃድ ፡ አዋጆች ፡[28] መንግሥቱ ፡ ፈልሳሚዎችን ፡ እንዲጠብቅ ፡ ያስች

27. ለምሳሌ ፡ አፄ ፡ ምኒልክ ፡ እ.አ.አ. በጥር ፡ ፴ ፡ ፲፱፻፰ ፡ ከሸመን ፡ ደፈር ፡ ፍራንኮ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ደ ፡ ጂቡቲ ፡ አ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ኩባንያ ፡ ጋር ፡ ባደረጉት ፡ ውል ፡ የሰጡትን ፡ ሞኖፖሊ ፡ ሥልጣን ፡ ይመለከቷል ።

28. የኢንዱስትሪ ፡ ፈቃድ ፡ አዋጅ ፡ እ.አ.አ. ፲፱፻፷፮ ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፺፪ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፴ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፴፭ ፤ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ንግድ ፡ አዋጅ ፡ (፲፱፻፷፮ ፡ እ.አ.አ.) ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፺፫ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፴ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፴፪ ፤ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ንግድ ፡ አዋጅ ፡ (፲፱፻፷፮ ፡ እ.አ.አ.) አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፺፬ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፴ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፴፪ ።

ሰው ፡ ይሆናል ።[29] በነዚሁ ፡ አዋጆች ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ የንግድ ፡ የኢንዱስትሪና ፡ ቱሪዝም ፡ ሚኒስቴር ፡ ፈቃዱ ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ አንድን ፡ የተፈለ ሰመ ፡ ጥበብ ፡ ወይም ፡ ዘዴ ፡ እንዳይጠቀምበት ፡ ሊከለክል ፡ ይችላል ።[30] ምናልባት ፡ ይህ ፡ ዘዴ ፡ ችግሩን ፡ ለጊዜው ፡ እንዲያቃልል ፡ የተደረገ ፡ ይሆናል ። ሆኖም ፡ የፈልሳ ሚውም ፡ ሆነ ፡ የሕዝቡ ፡ ጥቅም ፡ ተሟልቶ ፡ አልተጠበቀም ።

ከሁሉም ፡ የከበደው ፡ ችግር ፡ አንድ ፡ ፈልሳሚ ፡ ለፈለሰመው ፡ ነገር ፡ ጥበቃ ፡ እንዲደረግለት ፡ ሚኒስትሩን ፡ በጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ለመፍቀድ ፡ ለመከልከልም ፡ ሆነ ፡ የጠያቂውን ፡ መብት ፡ ለመወሰን ፡ የተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ ነው ። ባንድ ፡ በኩል ፡ ሚኒስትሩ ፡ ይህን ፡ ሥልጣን ፡ ፈልሳሚው ፡ የፈጠረውን ፡ ነገር ፡ ለሕዝቡ ፡ እንዲያስታ ውቅና ፡ ፈቃድ ፡ በግዴታ ፡ ያወጣ ፡ ዘንድ ፡ ሊያስገድድበት ፡ ይችላል ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ከሥልጣኑ ፡ አልፎ ፡ ሰው ፡ እየለየ ፡ ሊጠቅምበትና ፡ ሊጎዳበት ፡ ይችላል ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ ፈቃድ ፡ ጠያቂው ፡ ፈልሳሚ ፡ ከሚኒስትሩ ፡ ጋር ፡ በመጀመሪያ ፡ ስምም ፡ ቢሆን ፡ በኋላ ፡ ጥበቃው ፡ ይቀጥልለታል ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ሚኒስትሩ ፡ ገደቡን ፡ ወይም ፡ ስምምነቱን ፡ የሚጠብቅበት ፡ የጊዜ ፡ መጠን ፡ ስሌለ ፡ ፈቃዱን ፡ ይቀጥል ፡ ዘንድ ፡ የተጣለበት ፡ ግዴታ ፡ የለም ። ይህም ፡ ፈልሳሚው ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ጥበቃውን ፡ እንዲያራዝምለት ፡ ሊያስገድደው ፡ እንዲችል ፡ አያደ ርገውም ። ከዚህ ፡ የሚከተለው ፡ ችግር ፡ የተፈለሰመው ፡ ጥበብ ፡ የሚዳብርበትን ፡ ገን ዘብ ፡ ማግኘቱ ፡ ይሆናል ። ሊፈጠር ፡ የሚችለው ፡ ሌላው ፡ ችግር ፡ ደግሞ ፡ ፈቃድ ፡ የሚ መለከተው ፡ ፈቃድ ፡ ተቀባዩንና ፡ ሚኒስትሩን ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ፈልሳሚው ፡ በፈቃዱ ፡ ላይ ፡ የተደረጉትን ፡ ውሳኔዎች ፡ ለማስከበር ፡ ክስ ፡ በፈቃድ ፡ አውጭው ፡ ላይ ፡ ለማ ምጣት ፡ አለመቻሉ ፡ ነው ። ተወዳዳሪ ፡ ነጋዴዎች ፡ ሊያመጡ ፡ በሚችሉት ፡ የክስ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሌሎች ፡ ባለፈቃዶች ፡ ያላቸውን ፡ የመክሰስ ፡ መብት ለመስጠት ፡ ይነፍጉ ፡ ይሆናል ። ፈልሳሚው ፡ ሚኒስትሩ ፡ ፈቃዱን ፡ እንዲሠርዝ ፡ ቢያ ግባባው ፡ ወይም ፡ በባለፈቃድ ፡ አውጭው ፡ ላይ ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ ቢያቀርብበት ፡ እንኳ ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ እርምጃ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በፖለቲካ ፡ ምክንያት ፡ ሊዘገይና ፡ ድርድር ፡ ሊያስገባው ፡ ይችላል ።

---

29. ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ በግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ቁጥር ፡ ፳፰ ፡ በተጠቀሰው ፡ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ንግድ ፡ አዋጅ ፡ በአን ቀጽ ፡ ፫ ፡ ንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፡ እና ፡ በአንቀጽ ፡ ፮ ፡ መሠረት ፡ ከሆነ ፡ "ለማንኛውም ፡ የንግድ ፡ ሁኔታ" ፡ ሚኒስትሩ ፡ የፈቃዶችን ፡ ቁጥር ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ። ይህን ፡ ሰፊ ፡ ሥልጣን ፡ መግቻ ፡ እውነተኛው ፡ ገደብ ፡ ቁጥሮችን ፡ የሚወስኑ ፡ ደንቦች ፡ ማውጣቱ ፡ ነው ።

30. በሚኒስትሩ ፡ በተላለፈ ፡ ሴርኩለር ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ያለው ፡ የአመዘጋገብ ፡ ሥነ—ሥርዓት ፡ እንደሚ ከተለው ፡ ተገልጿዋል ፡—

> የኢንዱስትሪ ፡ ባለቤትነት ፡ መብትን ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ የምስክር ፡ ወረቀቶችን ፡ ለማግ ኘት ፡ የሚያመለክቱ ፡ ወዲያውኑ ፡ የቀደምትነት ፡ ምዝጋባዎችንና ፡ የማስጠንቀቂያ ፡ ማስታወ ቂያዎችን ፡ ማስገባት ፡ አለባቸው ፡ ... አንድ ፡ ማመልከቻ ፡ እንደገባ ፡ እንደያይነቱ ፡ ፍለጋ ፡ ይቀ ጥላል ፤ በስም ፡ ማስገቢያ ፡ ካርድ ፡ ውስጥ ፡ ለመዝገቡ ፡ የደረሱ ፡ ወይም ፡ የተመዘገቡ ፡ የባለንብ ረት ፡ ስሞችና ፡ የሚመሳሰሉ ፡ ወይም ፡ የሚያሳስቱ፡ምልክቶች ፡ ተለቅመው ፡ ይወጣሉ ። መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻዎችንና ፡ የተያያዙ ፡ መዝገቦች ፡ የተሟሉና ፡ ትክክል ፡ ሆነው ፡ ካገኛቸው ፡ ከታ ተመበት ፡ አንድ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ አመልካቹ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ይሰጠዋል ፤ ይኸውም ፡ የሚሆ ነው ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ባለቤትነት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት፡የተቀበላቸው፡ማመልከቻዎች ፡ አጠራጣሪ ፡ ካል ሆኑ ፡ ነው ።

ስለ ፡ ንግድ ፡ ምልክት ፡ ሴርኩለር ፡ ፩ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ (ጥር ፡ ፲፱፻፸፩ ፡ ኢ.አ.አ.) ፡ ገጽ ፡ ፩—፬.

በእንዱስትሪ ፡ በኩል ፡ የሚፈለሰሙትን ፡ ጥበቦች ፡ ለመጠበቅ ፡ ያሉን ፡ ሌሎች ፡ አስተሳሰባዊ ፡ ምርጫዎች ፡ በውጭ ፡ ሀገር ፡ ያሉትን ፡ የእንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ ባለቤትነት ፡ ሕጎች ፡ መሠረታዊ ፡ ጠባዮች ፡ አልያዙም ። እነዚህ ፡ ጠባዮች ፡ አንድ ፡ ፈልሳሚ ፡ ያገኘው ፡ ጥበብ ፡ እርግጠኛ ፡ "የተፈለሰመ" ፡ መሆኑን ፡ ለማረጋገጥ ፡ አንድ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ከመረመረለት ፡ በኋላ ፡ በሕዝብ ፡ መዝገብ ፡ እንዲያስ መዘግብና ፡ በተለየ ፡ የመንግሥት ፡ መጽሔት ፡ እንዲያስታውቅ ፡ ያደርጋሉ ። እንዲሁም ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ (ለምሳሌ ፡ ለእንዱስትሪ ፡ ጥበቦች ፡ ፍልሰማ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የአሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡) የሞኖፖሊ ፡ መብት ፡ እንዲሰጠው ፡ ያደርጋል ። እነዚህ ፡ ጠባዮች ፡ የወጡበት ፡ ዓላማ ፡ የፈልሳሚውንና ፡ እንዲሁም ፡ የሕዝቡን ፡ ጥቅሞች ፡ ሳያዛቡ ፡ በትክክል ፡ ለመያዝና ፡ እነዚሁ ፡ ጥቅሞች ፡ ሳይበደሉ ፡ በማመዛዘን ፡ የእንዱስ ትሪ ፡ ንብረት ፡ መብቶችን ፡ ለመጠበቅ ፡ ነው ። የእንዱስትሪ ፡ የንብረት ፡ መብትን ፡ ለማብራራትና ፡ ለመቆጣጠር ፡ የሚያስችለው ፡ ሕግ ፡ ራሱን ፡ ችሎ ፡ በመጠናቀቅ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

፬. <u>አስተዳደሩ ፡—</u>

በሚኒስትሮች ፡ ሥልጣን ፡ መግለጫ ፡ ትዕዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፬(መ) ፡ በትዕዛዝ ፡ ፵፮ እ.አ.አ. በ፲፱፻፷፯ ፡ ተሻሽሎ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ የንግድና ፡ ኢንዱስ ትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ በአዲስ ፡ አበባና ፡ በአሥመራ ፡ "የእንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ ባለቤትነ ትንና ፡ የንግድ ፡ ስም ፡ መዝገብ" ፡ አቋቁሟል ። የሚኒስቴሩም ፡ አጠቃቀሙን ፡ የሚ መለከቱ ፡ ሕጎች ፡ በማውጣት ፡ ሠራተኞቹ ፡ በዚህ ፡ መዝገብ ፡ እንዴት ፡ ለመጠቀም ፡ እንደሚቻል ፡ ልምምድ ፡ አግኝተዋል ። የእንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ መብትን ፡ የሚመ ለከት ፡ ሕግ ፡ ቢወጣ ፡ ያለብዙ ፡ ችግር ፡ ማስልጠንና ፡ ወጪ ፡ የኖረውን ፡ አሠራር ፡ ከሕጉ ፡ ጋር ፡ ማዋሀድ ፡ ይቻላል ።

## <u>መደምደሚያ ።</u>

ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የንግድ ፡ ስሞች ፡ አግባብ ፡ በሌለው ፡ ውድድር ፡ ክስ ፡ ቢከበሩም ፡ እንዲሁም ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አስተሳሰቦች ፡ መሠረት ፡ ሌሎችን ፡ የእ ንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ መብቶች ፡ ለማስከበር ፡ ቢችሉም ፤ በመጀመሪያ ፡ በንግድ ፡ ሕጉ ፡ እንደታየው ፡ ልዩ ፡ ሕግ ፡ ማውጣቱ ፡ ለብዙዎቹ ፡ ጥርጣሬዎች ፡ መፍትሔ ፡ እንደሚ ሆንላቸውና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የእንዱስትሪ ፡ ጥቅሞችን ፡ የሚመለከቱትን ፡ የተለዩ ፡ ችግሮች፡ በዝርዝር ፡ እንደሚቆጣጠር ፡ ይታመናል ። ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አንድ ፡ እንዱስ ትሪ ፡ ለምርምር ፡ (ሪሰርች) ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ለማጥፋት ፡ ስለማይችልና ፡ የውጭ ፡ ሀገ ርንም ፡ ቴክኖሎጂ ፡ ለማግኘት ፡ ስለማይችል ፡ "ልዩ" ፡ ሕግ ፡ መውጣቱ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ። ሆኖም ፡ የእንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ መብትን ፡ የሚጠብቅ ፡ ሕግ ፡ ቢወጣ ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ካፒታል ፡ ወደሀገሪቷ ፡ ይስባል ። እንዲሁም ፡ ልዩ ፡ ሕግ ፡ ቢወጣ ፡ የተ ፈለሰሙ ፡ ጥበቦችን ፡ በሀገሪቷ ፡ ውስጥ ፡ ከጥቅም ፡ ላይ ፡ እንዲውሉ ፡ የሚያደርገውን ፡ የካፒታል ፡ መሳብ ፡ እንደፈቃድ ፡ ማውጣት ፡ ካሉት ፡ ግዴታዎች ፡ ጋር ፡ ሊያመጣጥን ፡ ይችላል ። ስለዚህ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የልማትና ፡ የንግድ ፡ መመሪያ ፡ በሚያወጣበት ፡ ጊዜ ፡ አጠቃላይ ፡ የሆነ ፡ የእንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ ሕግ ፡ ለማዘጋጀትና ፡ ለማወጅ ፡ አጥብቆ ፡ ማሰብ ፡ አለበት ።